# የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 እና 2

1)የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን ማን ጻፈው?
ሀ)ቴዎፍሎስ ለ)ቅዱስ ሉቃስ ሐ)ቅዱስ ማትያስ መ)መልስ አልተሰጠም

2)የሐዋርያት ሥራ ለማን ተፃፈ?
ሀ)ለቅዱስ ሉቃስ ለ)ለበርናባስ ሐ)ለቴዎፍሎስ መ)ለቅዱስ እስጢፋኖስ

3)ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ኃይልን እስኪቀበሉ በየት እንዲቆዩ አዘዛቸው?
ሀ)በገሊላ ለ)በኢየሩሳሌም ሐ)በሰማርያ መ) በሁሉም

4) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ምስክር ይሆኑበታል ብሎ ከተናገራቸው ከተሞች ውስጥ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ)ሰማርያ ለ)ይሁዳ ሐ)ኢየሩሳሌም መ) ባቢሎን

5)ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያረገው?
ሀ) እያዩት ከፍ ከፍ አለባቸው ደመናም ተቀበለችው
ለ) እየረቀቀ ነው ያረገው
ሐ) እንደ ኤልያስ በሰረገላ ነው
መ)ሁሉም

6) እንደ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያርግ ሐዋርያት ወደ ሰማይ ሲያዩ ያናገሩዋቸው ሁለት ነጭ የለበሱ ሰዎች
ሀ)ሙሴ እና ኤልያስ ናቸው
ለ)ፈያታዊ ዘየማን እና አዳም ናቸው
ሐ) አሮን እና ዕዝራ ናቸው
መ)ከመላእክት ወገን ናቸው

7) የሐዋርያት ሥራ 1
20፤ "በመዝሙር መጽሐፍ፡— መኖሪያው ምድረ በዳ ትሁን የሚኖርባትም አይኑር፤ ደግሞም፡— ሹመቱን ሌላ ይውሰዳት፥ ተብሎ ተጽፎአልና።"
ይህንን ትንቢት በብሉይ ኪዳን በየትኛው መጽሐፍ እናገኘዋለን?
ሀ)መጽሐፈ ሩት ለ)መዝሙረ ዳዊት ሐ)መጽሐፈ አስቴር መ)መጽሐፈ ሶስና

8)በሐዋርያት ሥራ የተጻፈው የአስቆሮቱ ይሁዳ አሟሟት እንዴት ያለ ነው?
ሀ) ታንቆ ሞተ
ለ) በግንባሩ ወድቆ ከመካከሉ ተሰነጠቀ
ሐ) አንጀቱ ተዘረገፈ
መ) ሁሉም

9)ሐዋርያት የይሁዳ ምትክ የሆነውን ሰው በምን መረጡ?
ሀ)መልኩ ያማረውን አይተው ለ)አንደበተ ርቱዕ የሆነውን ሐ)በእጣ መ)በድምፅ ብልጫ

10) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሸጠበት 30 ዲናር መጨረሻው ምን ሆነ?
ሀ)ይሁዳ ወስዶ ተጠቀመበት ለ)የሸክላ መሬት ተገዛበት ሐ)ወደ መቅደስ መባ ተጨመረ መ)ለቄሣር ተሰጠ

11)አኬልዳማ ማለት ምን ማለት ነው?
ሀ)የሐዋርያት ሲኖዶስ ለ)ወተት የምታፈልቅ መሬት ሐ)የአስቆሮቱ ይሁዳ መሬት መ)የደም መሬት

12)በአስቆሮቱ ይሁዳ ምትክ ከሐዋርያት እንደ አንዱ ሊሆኑ በሐዋርያት መካከል የቆሙት ማን እና ማን ናቸው?
ሀ)ዮሴፍ እና ማትያስ ለ)ሉቃስ እና ማትያስ ሐ)ማርቆስ እና ማትያስ መ)ሁሉም

13)ጌታችን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካረገ በሓላ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 ላይ በጸሎት ሲተጉ አብረው ከነበሩት ውስጥ የሚመደበው/የምትመደበው ማን ነው/ናት?
ሀ)ቅድስት ኤልሳቤጥ
ለ) ጌታችን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ሐ)ካህኑ ዘካርያስ
መ)እመ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም

14)መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት በምን አምሳል ወረደ?
ሀ)በእሳት ለ)በውሃ ሐ)በሰው መ)በርግብ

15)ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ በሞላባቸው ጊዜ
ሀ)እየዘለሉ አመሰገኑ ለ)ትንቢትን ተናገሩ ሐ)በሀገሩ ሁሉ ቋንቋን ተናገሩ መ)ለ እና ሐ

16) በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 ሐዋርያትን የጉሽ ጠጅ ጠግበው ሰክረዋል እንዲሉ ያደረጋቸው ምን ነበር?
ሀ)ሐዋርያት እየዘለሉ ስላመሰገኑ
ለ)በሀገሩ ቋንቋ ስለተናገሩ
ሐ)መጥፎ ትንቢትን ስለተናገሩ
መ)ሁሉም

17)ጌታችን ካረገ በሓላ የመጀመርያውን ስብከት የተናገረው ማን ነው?
ሀ) ቅዱስ ዮሐንስ ለ)ቅዱስ ማትያስ ሐ)ቅዱስ ቶማስ መ)ቅዱስ ጴጥሮስ

18)በመጀመሪያው ስብከት ስንት ሰዎች አመኑ?
ሀ)4000 ለ)3000 ሐ)2000 መ)1000

19) በመጀመሪያው ስብከት ያመኑ ሰዎች ምን እናድርግ ባሉ ጊዜ ሊቀ ሐዋርያት ምን አላቸው?
ሀ)ስላመናችሁ ድናችኋል ሂዱ አላቸው ለ)ንስሓ ግቡ ሐ)ተጠመቁ መ)ለ እና ሐ

20)ሐዋርያት አዲስ አማኞቹን በማን ስም አጠመቋቸው?
ሀ)በአብ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም
ለ)በኢየሱስ ክርስቶስ ስም
ሐ)በሐዋርያው ስም
መ)በተጠማቂው ስም